

# የመነጠቅ፣ የመከራው ዘመን፣ የቅድስቲቱ ከተማ እና የእግዚአብሔርና የሰይጣን ዙፋኖች ራዕይ

## ኢየሱስ ክርስቶስን ያየች የ8 ዓመት ልጅ ምስክርነት

## (ያኔት ባልዴራስ ካኔላ)

*በመጀመሪያ በስፓኒሽ ድምጽ ቅጂ የተገኘ ሲሆን ገለጻዎች/ስዕሎቹ የምስክርነቱ ክፍል ሳይሆኑ በኋላ ላይ የተጨመሩ ናቸው። ይህ ምስክርነት ገለልተኛና ታማኝ በሆነ ነቢይ ተረጋግጧል። (www.DivineRevelations.info)*

ውድ ወንድሞች እግዚአብሔር ሁላችሁንም በዚህች ሠዓት ይባርካችሁ። እስቲ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይህንን እናንብብ 2ኛ ቆሮንጦስ 12፥1-4 የእግዚአብሔር ቅዱስ ቃላት። በስመአብ፥ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ “*ትምክህት የሚያስፈልግ ነው፤ አይጠቅምም ነገር ግን ከጌታ ወዳለው ራእይና መገለጥ እመጣለሁ። ሰውን በክርስቶስ አውቃለሁ፥ በሥጋ እንደሆነ አላውቅም ወይም ከሥጋ ውጭ እንደሆነ አላውቅም፥ እግዚአብሔር ያውቃል፤ እንዲህ ያለው ሰው ከአስራ አራት ዓመት በፊት እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ ተነጠቀ። እንዲህ ያለውን ሰው አውቃለሁ፥ በሥጋ እንደሆነ ወይም ያለ ሥጋ አላውቅም፥ እግዚአብሔር ያውቃል፤ ወደ ገነት ተነጠቀ፥ ሰውም ሊናገረው የማይገባውን የማይነገረውን ቃል ሰማ።*”

ይህን እኔ በሴፕቴምበር 5፥1999 እ.ኤ.አ ከጌታ ጋር ከነበረኝ ገጠመኝ ጋር አያይዝላችኋለሁ። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነበርን እናም የእግዚአብሔር ኃይል ህይወታችንን እየሞላት በዚያ ነበር። በወለሉ ላይ ወደቅሁ እናም የጌታ በውስጤ መኖር ይሰማኝ ነበር። ጌታ በእኔ እየሠራ እንደሆነ ይሰማኛል፥ እናም ራእይ ያሳየኝ ጀመር።

በአንዱ ራእይ፥ ሁለት መንገዶችን አየሁ፥ አንደኛው ሰፊ ሆኖ ብዙ ሰዎች ይሄዱበታል፥ ግን እየሄዱ ያሉት ወደ ጥፋታቸው ነው። ሌላኛው መንገድ በጣም ጠባብ ነው፥ ብዙ ሰዎች ጌታን እያመሰገኑና እያከበሩ በእርሱ ላይ ሲሄዱ አየሁ።



ከዛም ጌታ መልአክ ከዘንዶ ጋር ሲዋጋ ሌላ ራእይ አሳየኝ። ዘንዶው አጋንንትንና እሳትን ወደዚህች ምድር ወረወረ።

ከዛ በኋላ በሌላ ራእይ ደማቅ የሚያንጸባርቅ የግድግዳ ሠዓት አየሁ። ከወርቅ የተሠራ ነበር። አስራ ሁለተኛው ሠዓት ላይ ያሳይ ነበር። ነገር ግን የሆነ እጅ ወደ አስራ አንድ ሠዓት ሲመልሰው አየሁ። ጌታ እንዲህ አለኝ “*ተመልከች አገልጋዬ፥ ሠዓቱን ወደ ኋላ የመለስኩት ህዝቦቼ እኔ እንደምፈልገው ስላልተዘጋጁ ነው፤ ሠዓቱን ወደ ኋላ የምመልሰው ህዝቦቼ እኔ እንደምፈልገው ስለማያመሰግኑኝ ነው፤ ለዛ ነው፥ በታላቁ ምህረቴ ምክንያት በእግሬ ላይ ለሚወድቅ ሁሉ ዘላለማዊ ህይወት እንዲያገኝ የመጨረሻ እድል እየሰጠሁ ነው።*”



ከዚያም እዛው መሬት ተኝቼ እያለሁ ጌታ ሌላ ራዕይ አሳየኝ። የሆነ ሰው ወደ እኔ ፈረስ እየጋለበ አየሁ። እጁን ዘረጋና እኔ ወደ ተኛሁበት ወደ መሬት ቀረበ። ከዛም ጌታ ወደ ክንዶቹ ውስጥ ሲወስደኝ ተሰማኝ። መንፈሴን (ነፍሴን) ወደ ክንዱ ሲወስዳት ተሰማኝ። ከዛ መጋለብ ጀመርን፥ ወደ ላይ ጋለብንና በጣም ከፍም ዝቅም ያላለ ቦታ ስንደርስ ቆምን። እንዲህ አለኝ "*የእኔ አገልጋይ ተመልከቺ፥ ከእኔ ጋር እንደምወስድሽ ነግሬሻለሁ፥ ያንን ነው እያደርግሁ ያለሁት፥ በአንደበቴ የተናገርኩትን እፈጽመዋለሁ። ያልኩትን አደርገዋለሁ። ለዚህ ነው እዚህ ያመጣሁሽ አገልጋዬ። መጀመሪያ ግን ለእናንተ ያደረኩትን ከግምት እንድታስገቢውና መቼም እንዳትረሺው ቁስሌን አሳይሻለሁ።*"

የእግዚአብሔር ዙፋን ያለበት ቦታ ደረስንና ጌታ ሚስማሮቹንና ጎኑ የተወጋበትን ቦታ አሳየኝ። እንዲሁም እንዴት እንደተገረፈ አሳየኝ። ለእኛ ብሎ የተቀበለውን ሰንበሩንና ቁስሉን አየሁ። "*ተመልከች የእኔ አገልጋይ፥ አብዛኞቻችሁ እኔ ያደረግሁላችሁን ነገር ሁሉ አታስቡትም፥ አብዛኞቻችሁ እኔ በመስቀል እንደሞትክሁላችሁ ረስታችኋል፥እናም አገልጋዬ ህመም ይሰማኛል። ህዝቦቼ ሲክዱኝ ያመኛል፥ልክ ያን ቁስል ድጋሚ እንደሚከፍቱት ያህል፥ እናም በጣም ነው የሚያመው። ልክ መስቀል ላይ በድጋሚ እንደሚሰቅሉኝ ያህል።*" ጌታ እንዴት እንደሚያለቅስ አየሁ፥ምክንያቱም እኛ ስናሳፍረው ህመም ይሰማዋል።

# - ገነት -



"*ለህዝቤ ያዘጋጀሁላቸውን ታላቅ ክብር ትነግሪያቸው ዘንድ ብዙ ነገር አሳይሻለሁ አገልጋዬ፥የወርቁን ጎዳናና የጠራውን ውኃ አሳይሻለሁ*" አለኝ።

ብዙም ሳንቆይ የሚያምር ጎዳና ያለበት ቦታ ደረስን፥ በጣም ያምራል። በምድር ላይ እንደዚህ ዓይነት ነገር አይቼም ሆነ ነክቼ አላውቅም። ጎዳናዎቹ አንጸባራቂ ነበሩ። እንዲህ አለኝ "*የወርቁን ጎዳና ንኪው አገልጋዬ፥ ምክንያቱም አንቺና ህዝቤ በዚህ ትኖራላችሁ፥ ምክንያቱም ህዝቤ በዚህ ይጋልባሉ።*" የራሴንና የጌታን ነጸብራቅ ስንጋልብ አየሁ።

ከዛ በኋላ የጠራው ውኃ ጋር ደረስን፥ በጣም ነበር የሚያምረው። በዚያ በውብ ሐይቅ
ውስጥ ከጌታ ጋር እየጋለብን ሳለ "*አገልጋዬ፥ ይህ ሁሉ ለእኔ አይደለም፥ ይህ ሁሉ ለህዝቤ ነው። ይህ የምትነኪው ሁሉ ለህዝቤ ካለኝ ታላቅ ፍቅር ያዘጋጀሁት ነው።*" ብሎ ነገረኝ። ከዛ ደግሞ እንዲህ አለኝ። "*አገልጋዬ፥ነይ ወደዚህና ሌሎች ነገሮችን አሳይሻለሁ።*"

ከዚያም የእግዚአብሔርን ክብር ማየት የቻልኩበትና ኃይሉ የተሰማኝ ቦታ ደረስን። ትልቅና የሚያምር ቦታ ነበር። ትልቅ ጠረጴዛ ስላየሁ ጌታን ጠየቅሁት "*ጌታ ሆይ፥ እነዚህ ሁሉ ጠረጴዛዎች ለመንድር ናችው?*" እርሱም እንዲህ አለኝ "*አገልጋዬ፥ የበጉን ሠርግ አስታውሺ፥ በዚህ ጠረጴዛ ላይ የበጉን ሠርግ እንደምናከበር አስታውሺ።*" የማይቆጠሩ ጠረጴዛዎችን አየሁ፥ መጨረሻውን እንኳን ማየት አልቻልኩም። በእያንዳንዱ ጠረጴዛ አጠገብ መላእክት አሉ፥ ስለዚህ ጌታን ጠየቅሁት "*ጌታ ሆይ፥ለምንድር ነው በእያንዳንዱ ጠረጴዛና በእያንዳንዱ ወንበር አጠገብ መልአክ ያለው?*" ጌታም "*አገልጋዬ፥ እነዚህ መላእክት ጠረጴዛዎቹን እያስጌጡ ነው፥እኔ ዝግጅቴን ስለጀመርኩ መላእክቱ እያንዳንዱን ጠረጴዛ እያዘጋጁ ነው።*"

ውድ ወንድሞቼ፥እነዚያ ጠረጴዛዎች በጣም አንጸባራቂ ናቸው፥ሁሉም ከወርቅ ነው የተሠሩት። ጠረጴዛዎቹ በጣም ቆንጆ ሆነው አሸብርቀዋል። እያንዳንዱ መልአክ ሹካዎችን፣ ቢላዎችን፣ ማንኪያዎችን፣ ሰሀኖቹን እንዴት እንደሚያስቀምጡ አየሁ፤ ሁሉም በወርቅ የተሠሩና የሚያማምሩ ናቸው። ጌታም እንዲህ አለኝ

“*አገልጋዬ፥ ለህዝቤ እንዲዘጋጁ ንገሪያቸው፥ ምክንያቱም በጣም በቅርቡ በበጉ ሠርግ አብረውኝ እንዲደሰቱ ከእኔ ጋር እወስዳቸዋለሁ።*”

በጣም የሚያምር ነበር፤ በዚያ ያለው የጌታ መኖር በውስጤ ይሰማችኋል፥ እንደዚህ ያለ ክብርና ግርማ! ጌታም እንዲህ “*አገልጋዬ፥ወደዚህ ነይ ሌላ ነገር አሳይሻለሁ።*” አለኝ። ብዙ የሚያማምሩ በሮች ወዳሉበት ቦታ ደረስን፥ በጣም ብዙ የሚያማምሩ በሮች። “*ጌታ ሆይ፥ ከእነዚህ በሮች ጀርባ ምንድን ነው ያለው?*” አልሁት። እርሱም እንዲህ አለኝ “*ከዚህ በር ጀርባ ያሉት ደቀመዛሙርቶቼ ናቸው፥ ከእነዚህ በሮች ጀርባ ያሉት ሐዋርያቶቼ ናቸው፥ ከእነዚህ በሮች ጀርባ የሆነ ጊዜ በምድር ላይ ስሜን ሲያመሰግኑና ሲያወድሱ የነበሩ ሰዎች አሉ።*”

# - ማርያም -



እንደገና መጋለብ ጀረመርንና በግማሽ ከተከፈተ በር ጋር ደረስን እናም ጌታ እንዲህ አለኝ “*አገልጋዬ ወደዚህ ነይ፥ ነይ ወደዚህ ምክንያቱም ከዚህ በር ጀርባ ያለችው ማርያም ናት። ጠጋ በይና የምትለውን ስሚያት፥ ስለዚህ ሄደሽ ለህዝቤ መንገር እንድትችዪ፥ ስለዚህ ማርያም እንዴት እየተሰቃየች እንደሆነ ለህዝቡ እንድትነግሪያቸው።*” ጠጋ አልኩኝና ወጣት ሴት አየሁ፥ በጣም የምታምር ወጣት ሴት፥ በጣም ቆንጆ ናት፥ መልኳ በጣም ውብ ነው። በትንሽዬ መስኮት በኩል እያየች ነበር። ተንበርክካ ወደ ምድር ገጽ እያየች ነበር፥በከባድ ህመም እያለቀሰች።

እንዲህ አለች “*ለምንድን ነው የምታመልኩኝ /የምታወድሱኝ/? እኔ ምንም ኃይል ከሌለኝ፥ ለምን! ለምንድን ነው የምታመልኩኝ? እኔ ምንም አላደርግም! አታምልኩኝ! በእኔ ፊት አትስገዱ! እኔ ላድናችሁ ስለማልችል! ሊያድናችሁ የሚችለው፥ሊቤዣችሁ የሚችለው ኢየሱስ ብቻ ነው፥ለሰው ልጅ ሁሉ የሞተው! ብዙ ሰዎች እኔ ኃይል እንዳለኝ ይናገራሉ፥ተዓምር ማድረግ እንደምችል፥ግን ይህ ውሸት ነው! እኔ ምንም አላደርግም! ሁሉን ቻዩ አምላክ በእኔ ስለተደሰተ ኢየሱስ ተወልዶ ሁሉን እንዲያድን ማህጸኔን ተጠቀመ፥ ነገር ግን እኔ ምንም ኃይል የለኝም። እኔ ምንም ማድረግ አልችልም! በእኔ ፊት አትስገዱ! እኔ አምልኮት (፣ምስጋና) ስለማይገባኝ አታምልኩኝ! የሚገባው ብቸኛው፥ ብቸኛው በፊቱ የምትሰግዱለትና የምታመልኩት /የምታደንቁት/ ኢየሱስ ነው! የሚፈውሰውና የሚያድነው እርሱ ብቻ ነው!*”

ያቺ ሴት በምን ዓይነት ከባድ ህመም ውስጥ በጭንቀትና በለቅሶ ተሞልታ እንዳለች ማየት ችዬ ነበር። እንዲህ አለች “*አይደለም! አይደለም! አታምልኩኝ (፣አታመስግኑኝ)! በእኔ ፊት የምትሰግዱት ለምንድን ነው? እኔ ምንም አላደርግም!*” አያችሁ ውድ ወንድሞቼ፥ ይህችን ሴት በእንደዚህ ያለ ህመምና ሀዘን ስታለቅስ ማየት ከባድ ነገር ነበር።

# -እጀጠባቦችና አክሊሎች-

ጌታ እንዲህ አለኝ “*አገልጋዬ ወደዚህ ነይ፥ ምክንያቱም ሌሎች ነገሮችን ላንቺ ማሳየቴን እቀጥላለሁ።*” በጣም የሚያምር ቦታ ደረስን፥ በዚያ የእግዚአብሔር ክብር ይሰማኛል። ነጫጭ እጀጠባቦችን በረድፍ በረድፍ ሆነው አየሁ፥ በጣም ነጭና የሚያምሩ! ነካኳቸው እናም ጌታ እንዲህ አለኝ “*አገልጋዬ፥ እነዚህን እጀጠባቦች ንኪያቸው ምክንያቱም ሁሉም ለእናንተ ለሁላችሁም ናቸው።*”

ብዙ ረድፎች አየሁ ለስላሳውንም ልብስ ነካሁ። በጣም የሚያበራና ነጭ ነበር፥ በምድር ላይ እንደሱ ዓይነት ነገር አልነካሁም። ጌታም “*አገልጋዬ፥ እነዚህ ልብሶች ለእናንተ ለሁላችሁ ናቸው።*” አለኝ። በጉንጮቹ ላይ እንባው ይፈስ ነበር። እንዲህ አለኝ ጌታ “*አገልጋዬ፥አብዛኞቹ እነዚህ ነጫጭ እጀጠባቦች የሚወስዳቸውን ሰው እየጠበቁ እዚህ ይቀራሉ። ብዙዎቹ እጀጠባቦች የሚወስዳቸውን ገላ እየጠበቁ እዚህ ይቀራሉ።*” “*ለምንድን ነው ጌታ ሆይ?*” ብዬ ጠየቅሁት። “*ምክንያቱም አብዛኞቹ እኔ እንደምፈልገው ስለማያመልኩኝ ነው፥ ብዙዎች እኔ ለማደርግላችሁ ነገር ትኩረት አይሰጡትም። አገልጋዬ፥አብዛኞቹ እነዚህ ነጫጭ ልብሶች እዚህ ይቀራሉ፥ ገላን እየጠበቁ፥ ምክንያቱም በመንግሥቴ ምንም ቆሻሻ ነገር አልቀበልም። በመንግሥቴ የምፈቅደው ለቅዱስ ነገር ብቻ ነው። በቃሌ እንደተጻፈው እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ።*” (1ኛ ጴጥሮስ 1:16)

ተመለከትሁ ብዙ እጀጠባቦችንም አየሁ፤ በእያንዳንዱ ላይ በወርቅ ስም ተጽፎባቸዋል። ትናንሾችና በመጠን የተለያዩ እጀጠባቦችን ነካሁ፥ እናም እንዲህ አልኩ “*ጌታ ሆይ፥ እነዚህን ትናንሾቹን ማነው የሚለብሳቸው?*” ጌታም መለሰ “*አገልጋዬ፥ ትናንሽ ልጆቼን አስታውሺ፥ ለሁሉም እንዳለኝ አስታውሺ፥ እኔ ለሰው የማዳላ አይደለሁም፥ እነዚህ ትናንሽ እጀጠባቦች ስሜን ለሚያመሰግኑ ትናንሽ ልጆቼ ናቸው፤ ወደ ቤቴ ሄደው ስሜን ማወደስ ለሚወዱ ትናንሽ ልጆቼ፥በመሆኑም ለእነርሱ ትላልቅ ነገሮችን አዘጋጅቼላቸዋለሁ። እኔን ለሚፈልገኝ ሁሉ አለኝ፥ከእግሮቼ በታች ለሚመጡት ሁሉ አለኝ፥ዘላለማዊ ህይወትን እሰጣቸዋለሁ።*”



እንደገና መጋለብ ጀመርንና ብዙም ሳንቆይ ብዙ አክሊሎች ያሉበት ትልቅ ቦታ ደረስን። የቅንጦት የሆኑ አክሊሎች፥ አንጸባራቂ አክሊሎች፥ ስለዚህ “*ኦ ጌታ ሆይ! እነዚህ አክሊሎች፥ በጣም ያምራሉ። እነዚህ አክሊሎች ለማን ናቸው?*” አልሁት። ጌታም እንዲህ አለኝ “*አገልጋዬ፥ እነዚህ የምትነኪያቸው አክሊሎች፥ ስሜን ለሚያመሰግኑት ናቸው፥ እኔ እንደምፈልገው ስሜን ለሚያወድሱት ናቸው።*”

ጌታም ሌሎች አክሊሎችን አሳየኝ፥ ነገር ግን እነዚህ ምንም ጌጥ የለባቸውም። ከዛም ጌታ እንደዚህ አለኝ “*አገልጋዬ ወደዚህ አቅጣጫ ተመልከቺ።*” እናም ሌሎች አክሊሎችን ማየት ጀመርኩ፥ ነገር ግን እነዚህኞቹ የተሰሩት ከእሾኽ ነበር፤ ስለዚህ እንዲህ አልኩኝ “*ጌታ ሆይ፥ የሾኾቹንም ሆነ ጌጥ የሌለባቸውን አክሊሎች ለእኔ እንዲሆኑ አታድርግ!*” ጌታም አለኝ “*አገልጋዬ፥ በዚህ ቦታ ሦስት ዓይነት አክሊሎች አሉ፤ የቅንጦት የሆኑትና የሚያንጸባርቁት ስሜን የእውነት ለሚያመሰግኑኝ ናቸው፥ በእውነትና በፍጹም ልባቸው ስሜን ለሚያወድሱትና ለሚያመሰግኑት። በወይኔ እርሻ ውስጥ ለሚሠሩ፥ በቤቴ መሆንን ለሚወዱ፥ ስለስሜ ማራኪ ሆነው ለመገኘት ለሚሞክሩና መከራን ለሚቀበሉ። እነዚህ የምትነኪያቸው ምንም ጌጥ የሌለባቸው ደግሞ በቃሌ ለሚያሾፉ ነው፥ በቤቴ መሆን ፥ መጸም ለማይወዱ፥ እንዲሁም መጽናትን፥ አልያም ስሜን ማወደስ ለማይወዱ፤ በከንፈራቸው ብቻ እንጂ እኔ እንደምፈልገው ከልባቸው ለማያመሰግኑኝ። ለምን መሰለሽ አገልጋዬ፥ ምክንያቱም ማንም*



*እኔን ስለማያታለኝ፥ ከእኔ መደበቂያ ቦታ የለም። እነዚህ የምታያቸውና የምትነኪያቸው የእሾኽ አክሊሎች ደግሞ አገልጋዬ፥ በቃሌ ለሚቀልዱ ነው፥ ቃሌን ለሚያቃልሉ ነው፥ የልባቸውን በር ለማንኳኳው ነገር ግን ቃሌን ለመቀበል ፈቃደኛ ላልሆኑ ነው፥ ቃሌን ለሚያቃልሉ ሁሉ።*"

# -የመነጠቁ ራእይ-



ከዛ በኋላ ጌታ "*መነጠቁን አሳይሻለሁ፥ አመጣጤ እንዴት እንደሚሆን አሳይሻለሁ።*" አለኝ። ስለዚህ እኔም "*ጌታ ሆይ፥ እስካሁን ብዙ ነገር አይቻለሁ ለምንድን ነው ተጨማሪ ነገር የምታሳየኝ?*" አልኹት። ከዛም የእግዚአብሔር ዙፋን ጋር ደረስን፥ በዛ ሺሆችና ሺሆች መላእክት ተሰብስበው አየሁ። ከዛ ወደታች መሄድ ጀመርንና፥ እኔና ጌታ በጣም ነጭ የሆነ ደመና ውስጥ ቆምን። ጌታ ለመላእኩቱ ቤተ ክርስቲያንን እንዲቀበሏት ትእዛዝ ሰጠ፥ እናም ጌታ እንዲህ አለኝ "*በጥንቃቄ ተመልከቺ አገልጋዬ፥ ምክንያቱም ስመጣ እንደዚህ ነው የሚሆነው፥ አመጣጤ እንደዚህ ነው የሚሆነው።*"



ከአራቱም የምድር ማዕዘናት ሰዎች የጌታን ስም እያመሰገኑ ሲነሱ አየሁ። ሁሉም ሰዎች በእግዚአብሔር ኃይል ተሸፍነው ነበር። ነጫጭ እጀጠባቦችን ለብሰው ወደላይ ከፍ ከፍ ይሉ ነበር። በጣም ደስ የሚል መዝሙር ይዘምሩ ነበር "*ኦ ጌታ ሆይ፥ አንተ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ ነህ! አባት ሆይ እናመሰግንሀለን፥ አስነስተኸናልና! ጌታ ሆይ እናመሰግንሀለን፥ አንስተኸናልና!*"

ብዙ ዓይነት ሰዎች አየሁ ረዥም፣ አጭር፣ ጥቁር፣ ነጭ። ሁሉም ሰዎችና መላእክት እኔና ጌታ ወደ ነበርንበት ደመና ወደ ላይ ወጡ። ሁሉም መላእክትና ሰዎች ለጌታ በምስጋና ተሞልተው ነበር፥ እናም ሁላችንም እንዲህ አልን "*ኦ ጌታ ሆይ፥ አንተ ቅዱስ! ቅዱስ! ቅዱስ ነህ!*" እጅግ አስደናቂ ነገር ነበር፥ የማውቃቸው የመሰለኝ ብዙ ሰዎችን አየሁ። ሁሉም በእግዚአብሔር ክብር ተሞልተው ነበር።

# -የመከራው ዘመን ራእይ-

ከዚያ በኋላ የእግዚአብሔር ዙፋን ጋር ደረስንና ጌታ እንዲህ አለኝ "*አገልጋዬ፥ ነይ ወደዚህ።*" ከዙፋኑ ክፍል ወጣንና በጣም ትንሽ መስኮት ወዳለበት ቦታ ደረስን። ጌታም "*አገልጋዬ፥ አሁን ወደታች ተመልከች።*" አለኝ። በጣም ዘግናኝ ጥፋት አየሁ፥ አስከፊ ጥፋት፤ ምድር ሁላ ጠፍታለች እናም በመከራ ተሞልታለች። ጌታም እንዲህ አለኝ "*ተመልከች አገልጋዬ፥ ህዝቤን ከምድር ካወጣሁ በኋላ እንዲህ ነው የሚሆነው፥ ይህ ከምጽአቴ በኋላ ነው፥ ይህ የሚሆነው ቤተ ክርስቲያኔ እዚህ ከእኔ ጋር ሳለች ነው።*" አስከፊ መከራን አየሁ።

የሆነ ሠዓት ላይ ሰዎች ሲደሰቱ አየሁ፥ ነገር ግን ከዛ አባት ወንድ ልጁን ሲፈልግ፥ እናት ሴት ልጇን ስትፈልግ አየሁ፤ ነገር ግን ሊያገኟቸው አልቻሉም፥ ምክንያቱም ሁሉን ቻዩ አምላክ ወስዷቸዋል። ዘመድ

ዘመዱን ይፈልግ ነበር፥ ነገር ግን ሊያገኟቸው አልቻሉም። ሰዎች ጎረቤቶቻቸውን እየፈለጉ ነበር፥ ነገር ግን ሊያገኟቸው አልቻሉም፥ ምክንያቱም ጌታ ከእርሱ ጋር ወደ ላይ ወስዷቸዋልና።

በምድር ሁሉ ላይ አስከፊ ነገር እየሆነ ነበር። አንድ ፓስተር (ካህን) ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ሲሮጥ አየሁና ጌታን እንዲህ ብዬ ጠየቅሁት "*ጌታ ሆይ፥ ያ ሰውዬ ለምንድን ነው ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚሮጠው?*" ጌታም መለሰ "***አገልጋዬ፥ ይህ ሰው ፓስተር (ካህን) ነበር፥ ነገር ግን እንደምዘገይ ስላሰበ ከኋላ ተትቷል። እኔ አሁን እንደምመጣ አላሰበም፥ ከረዥም ጊዜ በኋላ ተመልሼ የምመጣ መስሎት ነበር፥ ለዛ ነው ከኋላ የቀረው።***" ፓስተሩ (ካህኑ) እንዲህ እያለ በየቦታው ይሮጥ ነበር "*ጌታ ሆይ፥ ለምንድን ነው ከኋላ የቀረሁት? ፓስተር (ካህን) ከሆንኩ፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስልጣን ካለኝና፥ ቤተ ክርስቲያን (ምእመናኑ) ከሄዱ፥ እኔ ለምንድን ነው የቀረሁት?*" ጌታ እንዲህ አለኝ "***አገልጋዬ፥ አሁን ምንም ማድረግ አልችልም፥ የምዘገይ መስሎት ነበር፥ በመሆኑም ቀርቷል።***"

ያ ሰው እንዴት እንደሚሰቃይ አየሁ። "*አሁን የምፈልገው ከክርሰቶስ ጋር መሄድ ብቻ ነው! የምፈልገው ብቸኛው ነገር ከጌታ ጋር መሆን ብቻ ነው ምክንያቱም እዚህ ሆኜ በታላቁ መከራ መሰቃየት አልፈልግም!*" አለ። ከቦታ ወደ ቦታ መቅበዝበዙን ቀጠለ፥ ራሱን እንዲህ እያለ ይጠይቅ ነበር "*ለምንድን ነበር የቀረሁት? ከአንተ ጋር ውሰደኝ ጌታ ሆይ! እዚህ ሆኜ መሰቃየት አልፈልግም!*" ጌታ እንዲህ አለኝ "***አገልጋዬ፥ አሁን ምንም ማድረግ አልችልም፥ ለረዥም ጊዜ አናግሬዋለሁ እናም በጣም በቅርቡ እንደምመጣ ነግሬዋለሁ፥ ነገር ግን አላመነኝም፥ በመሆኑም አሁን ከኋላ ቀርቷል።***"



ብዙ ሰዎች በየቦታው ሲሮጡ አየሁ። ብዙ ሰዎች ግራ በመጋባት ሰላምን ፍለጋ በየቦታው ይሮጣሉ፥ ግን አያገኟትም። እንዲህ እያሉ ይጮኹ ነበር "*የህይወትን ቃል እንፈልጋለን! የእግዚአብሔርን ቃል ተጠምተናል!*" ነገር ግን ረፍዶ ነበር፥ ጌታ አንዴ ቤተ ክርስቲያንን (ምእመናንን) ከራሱ ጋር ወስዷል።

ብዙ ሴቶችንና ወንዶች ልጆችን በጫካዎች ውስጥ ሲሮጡ አየሁ፥ ሰላምን ፍለጋ በየተራራው ሲሮጡ። ሰላምን ይፈልጓታል ነገር ግን አያገኟትም። ጌታ ምክንያቱን ነገረኝ "***አገልጋዬ፥ አንዴ ቤተ ክርስቲያኔን ወስጃለሁ፥ አሁን የተቆጣጠረው ሰይጣን ነው።***" ሰይጣን ምድርን እየገዛ ነበር እና በምድር ሁሉ ላይ ስቃይ ነበር! ሰዎች ከቦታ ቦታ ይሮጡ ነበር። ሰዎች እርስ በእርሳቸው መበላላት ጸጉራቸውንም መነጫጨት ይፈልጉ ነበር። እርስ በእርሳቸው ይወቃቀሱ፥ እርስ በእርሳቸውም ይጎዳዱ ነበር፥ ምክንያቱም ሰላም ማግኘት ስለሚፈልጉ ነው፥ ነገር ግን ሊያገኟት አይችሉም! የማይቻል ነገር ነው ምክንያቱም ጌታ አንዴ ቤተ ክርስቲያኑን ወስዷታል።

በምድር ላይ እንደዚህ ያለ አስከፊ ጊዜ፥ እንደዚህ ያለ ዘግናኝ ነገሮች አየሁ። ብዙ ሰዎች እንደዚህ እያሉ እርስ በእርሳቸው ይጎዳዱ ነበር "*ፍቅር እንፈልጋለን! ሰላም እንፈልጋለን!*" ነገር ግን በጣም ረፍዷል! ጌታ እንዲህ አለኝ "***ተመልከች አገልጋዬ፥ አነጋግሬያቸዋለሁ፥ የሰዎችን ልብ እያንኳኳው ጊዜ አሳልፌአለሁ፥ ነገር ግን እነርሱ እኔን ሊፈልጉኝ አልወደዱም። ያው አሁን ኋላ ቀርተዋል፥ እኔ ምንም ላደርግላቸው አልችልም። ለምን፥ ምክንያቱም አንዴ ቤተ ክርስቲያኔን ከራሴ ጋር ወስጃለሁ። ሁሉም የእኔ ልጆች ከእኔ ጋር በበጉ ሠርግ ሲደሰቱ፥ እዚህ ያሉ ሰዎች ሁሉ ታላቅ መከራን ይቀበላሉ፥ እናም በዛ ለቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል። ቃሌን ለመፈጸም አይፈልጉም፥ ይልቁንም ቀልድንና ቃሌን ማቀለል መርጠዋል።***"

# -የሕይወት መጽሐፍ-



ከዛ በኋላ ጌታ የሚያምር ትልቅ መጽሐፍ አሳየኝ። በጣም የሚያንጸባርቅና ከውርቅ የተሠራ ነበር። “*ጌታ ሆይ፥ ያ ትልቁ መጽሐፍ፥ ለምንድን ነው?*” ብዬ ጠየቅሁት። እርሱም እንዲህ አለኝ “*አገልጋዬ፥ በዚህ መጽሐፍ ላይ እኔን የሚያመሰግኑኝ ስም፥ እና ንስሐ የገቡትና መንገዴን የሚፈልጉት ስም አለ። ይህ የሕይወት መጽሐፍ ነዉና። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስሜን ለማመስገንና በአምልኮ ከፍ ከፍ እያደረጉ ለማወደስ የሚሰበሰቡ ሁሉ ተጽፈዋል።*” መጽሐፉ ትልቅ ነበር እናም በወርቅ የተጻፉ ፊደላት አሉበት። እንዲህ አለኝ “*ተመልከች አገልጋዬ፥ ብዙዎቹ ስሞች በምህረቴ ምክንያት ያላጠፋዋቸው ናቸው፥ ምክንያቱም ብዙዎቹ ጀርባቸውን ሰጥተውኛል። ብዙዎች ጀርባቸውን ሰጥተውኛል፥ ነገር ግን ምህረቴ እጅግ ታላቅ ናትና እስካሁን አልሰረዝኳቸውም፥ ማንም እንዳይጠፋና የዘላለም ህይወት እንዲኖር ስለምፈልግ ነው።*” (ሕዝቅኤል 18፥31-32 *የምዋቹን ሞት አልፈቅድምና፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፤ ስለዚህ ተመለሱና በሕይወት ኑሩ።*) መጽሐፉን መንካት ጀመርኩ፥ እናም ብዙ ስሞች በውስጡ ተጽፈው አየሁ።

# -ሲዖል-

ከዛ በኋላ ጌታ እንደዚህ አለኝ “*አገልጋዬ፥ ሲዖልን አሳይሻለሁ።*” ስለዚህ እንደዚህ አልኩት “*ጌታ ሆይ አይሆንም! ልቋቋመው አልችልም፥ ያን ሁሉ ካሳየኸኝ በኋላ፥ በቃኝ።*” ከዛም ጌታም እንዲህ አለኝ “*አገልጋዬ፥ ሂደሽ ለቤተ ክርስቲያንና ሌሎችም ሰዎች ገነት እውን እንደሆነች ሁሉ ሲዖልም እውነት እንደሆነች ትነግሪያቸው ዘንድ፥ ሲዖልን አሳይሻለሁ።*” ቁልቁል ወደ ታች መሄድ ጀመርን። ገና ከሲዖል በጣም ሩቅ እያለን ነበር የጩኸትና የሰቆቃ ድምጽ መስማት የጀመርሁት። እንዲህ አልኩት “*ጌታ ሆይ ልቋቋመው አልችልምና ከዚህ ቦታ አውጣኝ!*” ጌታም መለሰልኝ “*ተመልከች አገልጋዬ፥ እኔ ካንቺ ጋር ነኝና አትፍሪ።*” በአንዳንድ ዋሻዎች ውስጥ ወደታች ሄድን። በዛ ቦታ ታላቅ ጨለማ ነበር፥ እዚህ ምድር ላይ ተሰምቶኝ የማያውቅ ዓይነት ጨለማ።

በአንዳንድ ግድግዳዎች አጠገብ አለፍንና ብዙ ነፍሳት ሲጮኹ ሰማሁ፥ የህመምና የሰቆቃ ጩኸት። ጌታም “*አገልጋዬ ወደ ፊት እንሂድ።*” አለኝ። የሚጮኸ ሰውዬ ወዳለበት ቦታ ደረስን። ጌታን ጠየቅኹት “*ጌታ ሆይ፥ ለምንድን ነው እዚህ ጋር የቆምነው?*” እርሱም መለሰ “*ተመልከች አገልጋዬ፥ ይህችን ሰው በጥንቃቄ ተመልከቺ፥ ምክንያቱም ይህች ሰው በምድር ላይ ዘመድሽ ናት።*” እና እኔም እንዲህ አልኩት “*ጌታ ሆይ፥ የትኛዋ? ላውቃት አልቻልኩም።*” ጌታም እንዲህ አለ “*ይህች ሰው በምድር ላይ አያትሽ ነበረች፥ ዘመድሽ ነበረች፥ ነገር ግን የማታምን ነበረች፥ ለዚህ ነው አሁን በዚህ ያለችው።*”



እንዲህ አለች “*እባክሽ ውኃ ስጭኝ፥ ከዚህ ቦታ አውጭኝ፥ ምክንያቱም ልቋቋመው አልቻልሁም፥ ተጠምቻለሁ።*” ነገር ግን ምንም ማድረግ አልቻልኩም፥ ላደርገው የቻልኩት ነገር ማልቀስ ብቻ ነው። “*ጌታ ሆይ፥ በማያልቀው ምህረትህና በማያልቀው ቸርነትህ፥ ከዚህ አውጣት!*

*ቤተሰቦቹ በገነት እንደሆነች ከነገሩኝ እዚህ ምን ትሠራለች?"*

ጌታም አለኝ "***አገልጋዬ፥ ካህኑ ለቤተሰቦችሽ ወደ ገነት እንደሄደች ነግሯቸው ነበር፥ ነገር ግን ውሸት ነው። ያ ውሸት ነው፥ምክንያቱም እርሷ በምስሎች ፊት ትሰግድ ነበር፥ምስላትን/ስዕላትን አመለከች፥እናም ተመልከች እነዚያ ምስሎች እንዴት ሊያድኗት እንዳልቻሉ። እንድትከፍትልኝና ወደ ውስጥ እንድገባ ብዙ ጊዜ ልቧን አንኳኳሁ፥ ይልቁን ግን በቃሌ ቀለደች። ስሜን ከማክበር ይልቅ ዓለምን መከተል የተሻለ እንደሆነ መረጠች፥ ለዚህ ነው በእዚህ ያለችው። ፈጽሞ ቃሌን ለመቀበል አልፈለገችም፥ ፈጽሞ ንስሐ መግባት አልፈለገችም፥ እናም ካህኑ ወደ ገነት እንዳረገችና አሁን በገነት አስደናቂ ቤቶች ውስጥ እንዳለች ነገራቸው፥ ነገር ግን ያ ውሸት ነበር። የት እንዳለች ተመልከች አገልጋዬ።"*** በከባድ ስቃይ እያለቀሰች ነበር። እንዲህ አለች "*ውኃ ስጡኝ! ከዚህ ቦታ አውጡኝ!"* ጌታም እንዲህ አለ "***አገልጋዬ፥አሁን ምንም ማድረግ አልችልም፥ ይህች ነፍስ ከእንግዲህ ለእኔ የተገባች አይደለችም።"*** ፊታችንን አዙረን ወደ ሌላ ቦታ ሄድን። ወደ እኔ ጮኸች "*አይሆንም! እዚህ አትተዉኝ! ውኃ ስጡኝ! ከዚህ ቦታ አውጡኝ!"* ምንም ሊያደርግላት አይችልም።

ወደ ብዙ ሰዎች መመልከት ቀጠልን። ነፍሳት "*ከዚህ ቦታ አውጣን!"* እያሉ የጌታን ልብስ ለመያዝ ሞከሩ። እርሱ ግን እንዲህ አላቸው "***ከእኔ ራቁ፥ ምክንያቱም ከዚህ በኋላ ለእኔ የተገባችሁ አይደላችሁም፥ የሰይጣንና የአጋንንቱ ናችሁ።"*** ብዙ ነፍሳት ብዙ ሰዎች ያሉበት በጣም ዘግናኝ ቦታ ነበር።

# -የሰይጣን ዙፋን-

መጋለባችንን ቀጥለን ዘግናኝ የሆነ ቦታ ደረስ፥ ጌታም እንዲህ አለኝ "***አገልጋዬ፥ተመልከች የሰይጣንን ዙፋን አሳይሻለሁ።"*** እኔም እንዲህ አልኩት "*ጌታ ሆይ፥አይሆንም! ያን ዙፋን ማየት አልፈልግም!"* እርሱም መለሰ "***እኔ ከአንቺ ጋር ነኝና አትፍሪ።"*** ከዛም አስከፊና አስቀያሚ ቦታ ደረስን። እጅግ ግዙፍ ወንበር ሰይጣን ተቀምጦበት አየሁ። ትላልቅ ጥፍሮች ነበሩት፥ ከት ብሎ ይስቃል፥ ሳቁን ሊያቋርጥ አልቻለም። እንዲሁም በየቦታው አጋንንትንም አየሁ። የተለያየ መጠን ያላቸውን ጌኖች፣ አጋንንትን፣ ሰይጣናትን እንዲሁም ብዙ የተለያዩ አጋንንትን አየሁ። ሰይጣን ለአጋንንቱ እንዴት ትእዛዝ እንደሚሰጣቸው አየሁ፥ወደ ላይ ወደ ምድር ሄደው ምድር ላይ ክፉ ነገር እንዲፈጠሩ እንዲያደርጉ።



እነዚያ አጋንንት ወደ ላይ ሄደው፥ የመኪስከስ አደጋ፣ መተራረድ፣ ጠብ፣ መፋታት፣ እና ሁሉም ዓይነት ክፉ ድርጊቶችን ሲፈጽሙ አየሁ። ከዛም ተመልሰው ወደ ታች ይመጡና ሁሉንም ያደረጉትን ነገር ለእሱ ይናገራሉ። ከዛ ሰይጣን ከት ብሎ ይስቃል። ሰይጣን ለአጋንንቱ ሽልማትን ሰጣቸው፥ ሰይጣኖቹም ያከብሩት፣ ያመሰግኑትና ይዘፍኑለት ጀመር።

ሰይጣን ክርስቲያኖችን ለማጥፋት ምን ያህል ብዙ እቅዶች እንዳሉትና፥ የእግዚአብሔርን አገልጋዮች ለማጥፋት ትልቅ እቅድ እንዳለው አየሁ። በዘመናዊነት የተሞሉ ትላልቅ ቤተ ክርስቲያኖችንና ምዕመናንን አየሁ። ጌታም እንዲህ አለ "***ተመልከች አገልጋዬ፥ እነዚህ ቤተ ክርስቲያኖች ሰይጣን ተቆራኝቷቸዋል፥ ስለዚህም ከእኔ ጋር መሄድ አይችሉም።"***

ጌታ አጋንንት ምን ያህል ብዛት ያላቸውን ግድያዎች እንደሚያነሳሱ አሳየኝ፥ እናም እነዚያ ሁሉ ነፍሳት ወደ ዘላለማዊ ፍርድ ይወድቃሉ፣ አስቀያሚ ቦታ። እቶንን አየሁ፥ እናም ጌታ "***ተመልከች አገልጋዬ፥ ይህ ነው የእሳቱ ባሕር፥ ይህ ነው ሲኦል።***"

አጋንንቱ መተራረድን ባነሳሱ ቁጥር፥ ሁሉም ነፍሳት ወደዚህ ቦታ ይወድቃሉ። እሳቱ ይውጣቸውና ይቀልጣሉ። ነፍሳቶቹ በህመምና በፍርሀት የጮኻሉ፥ እናም አጋንንቱ ወደ ሰይጣን ዙፋን መጥተው ያደረጉትን ይነግሩታል። ሰይጣን ከት ብሎ ይስቅና ለአጋንንቱ ሽልማትን ይሰጣቸዋል። አጋንንቱም ይዘሉለታ፣ የዘፍኑለታል እርሱን ለማስደሰት ሁሉንም ዓይነት ነገር ያደርጉለታል። ሰይጣንም ወደ ሲኦል በሚገቡት ነፍሳት ሁሉ በደስትና በኩራት ይስቃል። በየሰከንዱ መውደቃቸውን ቀጠሉ፥ ሰይጣንም በጣም ከመኩራቱ የተነሳ ሳቁን ሊያቆም አልቻለም።

በዚያ ቦታ ብዙ አጋንንትና ብዙ ጋኔሎች እንዳሉ ተረዳሁ። እንዲህ አልኩኝ "*ጌታ ሆይ፥ እባክህ ከዚህ ቦታ አውጣኝ፥ ከዚህ በኋላ ልቋቋመው አልችልም።*" አጋንንቱ እዛ ያሉትን ነፍሳት ይወጓቸውና ያሰቃዩአቸው ነበር። ነፍሳቱም ይጮኻሉ "*ብቻችንን ተዉን! በሰላም ተዉን፥ ሌላ ስቃይ አንፈልግም፥ ሰላም ነው የምንፈልገው!*" እናም ከዛ አጋንንቱ ይስቃሉ።

# -ቅድስቲቱ ከተማ-

ከዚያም ከዛ ቦታ ወጣንና ጌታ እንዲህ አለ "***ተመልከች አገልጋዬ፥ ያዘጋጀሁላቸውን አስደናቂ ስጦታ ትነግሪያቸው ዘንድ ቅድስቲቱን ከተማ አሳይሻለሁ።***" ወደ ላይ ወጣንና የሚያማምሩ ዛፎችና ረዣዥም ዝግባዎች ያሉበት የሚያምር ቦታ ደረስን። ሁሉም ነገር በጣም የሚያምር ነበር። የሚገርም የሰላም ስሜት ይሰማኛል።

በከተማዋ በር ውስጥ የሚያምር ቀስተደመና ነበር። በመንገዱ ሁለቱም አቅጣጫ ብዙ መላእክት ነበሩ። በበሩ ውስጥ አለፍን፥ እናም ጌታ እንዲህ አለኝ "***አገልጋዬ፥ ቅድስቲቱ ከተማ ይህች ናት።***" በሚያማምሩ ጽጌረዳዎች የተሞላ የአትክልት ስፍራ እስክንደርስ ድረስ ሄድን፥ በምድር ላይ ፈጽሞ እንደዚህ አይቼ አላውቅም።





የጌታን እጅ ለቅቄ ወደ አትክልት ስፍራው ሮጥኩ። አበባዎቹን አቀፍኳቸው፥ መዓዛቸው በጣም ጣፋጭ ነበር። አበባ ልቀጥፍ ነበር ነገር ግን ጌታ "***አይሆንም አገልጋዬ፥ ለአሁን ምንም መውሰድ አትችይም። እነዚህን አበባዎች መውሰድ የምትችይው ህዝቦቼ እዚህ ሲመጡ ብቻ ነው፥ ቤተ ክርስቲያኔ ወደዚህ ቦታ ስትመጣ፥ ያኔ እነዚህን አበባዎች ለመውሰድ ትችያለሽ።***" አለኝ። እኔም እንዲህ አልሁት "*ጌታ ሆይ፥ አንድ አበባ ብቻ ነው መውሰድ የምፈልገው፥ ከዛ ለሁሉም*

*አብያተ ክርስቲያናት አሳያቸዋለሁ።"* ነገር ግን ጌታ እንዲህ አለኝ "*አይሆንም አገልጋዬ÷ምክንያቱም ህዝቦቼ ገና በዚህ አይደሉም።"* በጣም ብዙ ዓይነት የሚያማምሩ አበባዎችን አየሁ።

ከዛ በሚያምር አረንጓዴ ሳር መሀል አለፍን። ጌታም በሳሩ ላይ ተቀመጠና ደስ በሚል ፈገግታ እንዲህ አለኝ "*አገልጋዬ÷ይህ የምትነኪውና የምታይው ሁሉ ለህዝቤ ያዘገጀሁት ነው።"* ከዛም ጋለብንና በፍራፍሬ ወደተሞላ ረዥም ዛፍ ደረስን። "*ጌታ ሆይ÷ ይህ ዛፍ? ይህ ዛፍ ምን ማለት ነው? እናም እነዚህ ሁሉ ፍራፍሬዎች?"* አሁንም አንድ ፍሬ ልቀጥፍ ነበር÷ነገር ግን ጌታ እንዲህ አለኝ "*አይሆንም አገልጋዬ÷አሁን እነዚህን ፍሬዎች መውሰድ አትችይም÷ ምክንያቱም ይህ ዛፍ የሕይወት ዛፍ ነው÷ እናም ህዝቤ ወደዚህ ወደላይ ሲመጡ ከዚህ ዛፍ ይበላሉ። ለጊዜው÷ ህዝቤ ወደዚህ ወደላይ እስኪመጡ ድረስ ምንም መውሰድ አትችይም።"* ዛፉ እጅግ የሚያማምሩ ፍሬዎች አሉት።

ከዛም መጋለባችንን ቀጠልን÷ ብዙ የሚያማምሩ ቢራቢሮዎችንና እንስሳትን አየሁ። ጌታም "*አገልጋዬ÷ ይህ እዚህ ያለው ነገር ሁሉ ለህዝቤ ነው። ለህዝቤ በጣም በቅርቡ በዚህ በቅድስቲቱ ከተማ እየጋለቡ እዚህ ቦታ እንደሚሆኑ ንገሪያቸው።"*

ቀጠልንና ብዙ ዛፎችና ዝግባዎች ያሉበት ሌላ የሚያምር ቦታ ደረስን። ጌታ እንዲህ አለኝ "*አገልጋዬ÷ ይህ ሁሉ ለህዝቤ ነው። አገልጋዬ÷ወደዚህ ነይ ድንቆችን አሳይሻለሁ።"*



በመላእክት የተሞላ የሚያምር ቦታ ደረስን። አንዱ መልአክ ግዙፍ ነበር÷ እናም በአፉ ትልቅ መለከት አለ። እንዲህ አልኩኝ "*ጌታ ሆይ÷ ያ መልአክ÷ ምን ማለት ነው?"* ጌታም መለሰ "*ተመለከች አገልጋዬ÷ ይህ መልአክ ትእዛዝ እየጠበቀ ነው÷ መለከቱን ለመንፋት እኔ የምሰጠውን ትእዛዝ እየጠበቀ ነው÷ እናም ይህ መልአክ መለከቱን መጫወት ሲጀምር÷ ህዝቤ ወደላይ ይወሰዳሉ÷ ይነሳሉ÷ እናም ይለወጣሉ። ነገር ግን ይህን እርግጠኛ ሁኚ አገልጋዬ÷ መለከቱ የሚሰማው ለሚጠባበቁት (ለሚመለከቱ) ብቻ ነው! ስለዚህ ሂደሽ ለህዝቤ እንዲመለከቱ ንገሪያቸው÷ለህዝቤ እንዳትተኙ ብለሽ ንገሪያቸው÷ምክንያቱም ከተኛችሁ መለከቱን አትሰሙም÷ ለህዝቤ እንዲመለከቱ ንገሪያቸው÷የተኙትን ወደ ላይ ላነሳቸው አልችልም።"*

መልአኩ በጣም ትልቅና የሚያምር ነበር÷ ከኋላውም ትናንሽ መለከት የያዙ ብዙ መላእክት ነበሩ። እነዚያ መለከቶች ከወርቅ የተሠሩና በጣም አንጸባራቂ ነበሩ። ጌታም አለኝ "*አገልጋዬ÷ ለህዝቤ መለከቱ እንዲሰማ ትእዛዝ ልሰጥ ስለሆነ÷እንዲዘጋጁ ንገሪያቸው።"*



እንደገና መጋለብ ጀመርን÷ እናም ጌታ እንዲህ አለ "*ተመልከች አገልጋዬ÷ የአባቴን ዙፋን አሳይሻለሁ። እስካሁን አላሳየሁሽም÷ አሁን ግን አሳይሻለሁ÷ ሂደሽ ለህዝቤ አባቴ እውነት እውን እንደሆነ እኔም እውነት እውን እንደሆንኩኝ ትነግሪያቸው ዘንድ።"* ሁላችንም መሄድ ጀመርን÷ ጌታ፣ መላእክቱና እኔ። ገና ከአብ ዙፋን ሩቅ እያለን÷ ከዛ በኋላ ልቋቋመው አልቻልኩም፤ ከእንደዚህ ዓይነት ኃይልና ግርማ ፊት መቆም አልቻልኩም። እየቀረብን እየቀረብን በሄድን ቁጥር÷ እንደ ላባ የሆንኩ ያህል ተሰማኝ÷ እርምጃዬን መቀጠል አልቻልሁም።

ከአብ ዙፋን ጋር ደረስን፥ እናም ከዙፋኑ ወደር የሌለው ኃይል ይሰማኝ ነበር። ኃይለኛ መብረቅ ከዙፋኑ መጣ፤ ባለ ግርማና ግዙፍ ነበር። ዙፋኑን የከበበ እንዲህ ያለ ኃይል፤ የሚያበራና ከወርቅ የተሠራ ነበር። የሆነ ሰው ዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ነበር፥ ነገር ግን ፊቱን ላየው አልቻልሁም፥ ከዙፋኑ የሚወጣውን ኃይል ልቋቋመው አልቻልኩም። አብ ከወገቡ በታች ብቻ ነበር የሚታየኝ። ነገር ግን ከወገቡ በላይ ላየው አልቻልኩም፥ ምክንያቱም ከዛ በኋላ በወለሉ ላይ ወደቅሁ። የወደቅሁበት ምክንያት እንደዚህ ያለውን ኃይልና ግርማ መቋቋም ስላልቻልኩ ነው።



ከዛ በኋላ 24 ሽማግሌዎች የጌታን ስም ሲያወድሱና ሲያመሰግኑ አየሁ። እንዲሁም ግዙፍ ሊቃነ መላእክት የጌታን ስም ሲያመሰግኑ አየሁ። 24ቱ ሽማግሌዎች እንዲህ እያሉ ተንበረከኩ "*አቤቱ አንተ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ ነህ!*" መላእክቱም ጌታን ሲያወድሱና ሲያመሰግኑ ፈጽሞ አይደክሙም፥ እንዲሁም ሽማግሌዎቹ የጌታን ስም ማወደሳቸውን አላቆሙም። ወደር የሌለው እሳት ከዙፋኑ ወጣ፥ በዙፋኑ ብዙ የሚያምሩ ነገሮች ነበሩ።



ከዛም ያን ቦታ ለቀን ወጣንና ግዙፍ መልአክ ወዳለበት ቦታ መጣን። እንዲህ አልሁኝ "*ጌታ ሆይ፥ ያ መልአክ ማን ነው?*" ጌታም መለሰ "***ተመልከች አገልጋዬ፥ ይህ መልአኩ ገብርኤል ነው፥ ይህንን ደግሞ ሌላኛውን መልአክ ተመልከቺ፥ ይህ ደግሞ ሚካኤል ነው።***" በጣም ትልቅና የተዋቡ ነበሩ። ጌታም እንዲህ አለ "***አገልጋዬ፥ ለህዝቤ መልአኩ ገብርኤልና መልአኩ ሚካኤል የእውነት እንዳሉ ንገሪ።***"



በኋላ ላይ ጌታ እንዲህ አለኝ "***አገልጋዬ፥ ነይ ወደዚህ፥ አለንጋውን አሳይሻለሁ።***" ጌታ ሦስት ጫፎች ያሉት አለንጋ ሲያወጣ ወዳየሁበት ሌላ ቦታ ደረስን። በጣም ትልቅ ወንበር መታበትና እንዲህ አለኝ "***አገልጋዬ ይሄ ለማይታዘዙት ነው፥ ይህ ለቃሌ መታዘዝ ለማይፈልጉት ነው። ቃሌን ስለማይታዘዙ በዚህ እገርፋቸዋለሁ፥ ምክንያቱም የምወዳቸውን እገርፋቸዋለሁ።***" ጌታ ወንበሩን በዚያ ጅራፍ እንዴት እንደመታ አየሁ እና እንዲህ አልኩኝ "*እባክህ አባዬ፥ በዛ አለንጋ እንዳትመታኝ!*" እርሱም መለሰልኝ "***እንግዲህ አገልጋዬ፥ ቃሌን ጠብቂ፥ ምክንያቱም የማይታዘዙትን እቀጣቸዋለሁ።***" (ራእ.3:19 *እኔ የምወዳቸውን ሁሉ እገሥጻቸዋለሁ እቀጣቸውማለሁ፤ እንግዲህ ቅና ንስሐም ግባ።*)

ከዚያም ጌታ ውብ ወደሆነ ቦታ ወሰደኝ፥ አስደናቂ ቦታ፥ በዛ ብዙ የወርቅ አክሊሎችን አየሁ። ነገር ግን እነዚያ አክሊሎች አስቀድሞ ስም ተጽፎባቸው ነበር፥ በፊርጥ የተሞሉም ነበሩ! ጌታም አለኝ "***ተመልከች አገልጋዬ፥ ይህ አክሊል ለአገልጋዬ ዪዬ አቪላ (Yiye Avila) ነው፥ ይህ ሌላኛው ደግሞ ለአገልጋዬ አርቱሮ ጋርሺያ (Arturo García) ነው።***" አክሊሎቹ ውድ ነበሩ! በአንዱ አክሊል ላይ እንዲህ የሚል ተጽፎ ነበር "አይዳ ቫዲሎ (**Aida Vadillo**)"፥ ሌላኛው "*ሚጉኤል ዱራን*(**Miguel Duran**)" የሚል አለበት፥ ሌላኛው "*አርማንዶ ዱራን*(**Armando Duran**)" የሚል አለበት፥ "*ጌታ ሆይ፥ አሁን የእነዚህን ሁሉ አገልጋዮች አክሊል ማየትና*

*መንካት እችላለሁ።"* እንዲሁም የ"ፓብሎ ፒንታዶ(Pablo Pintado)" እና "ናሁም ዛሙዲዖ(Nahum Zamudio)"ን አክሊል አየሁ።

ጌታም እንዲህ አለኝ "***አገልጋዬ÷ እዚህ እንድታዪ ፈቅጄልሻለሁ። ይህ በወይን እርሻዬ እየሠሩ ያሉትን አገልጋዮቼን አክሊል ላሳይሽ ነው÷እዚህ ነው ያደረኳቸው። ቃሌን እየሰበኩ ያሉትን አገልጋዮቼን ታዪ ዘንድ። ለእነርሱ ትልቅ ሽልማት አዘጋጅቼላቸዋለሁ።*** " ሺሆችና ሺሆች አክሊሎችን አየሁ÷ሁሉም ላይ ስም ተጽፎባቸዋል።



ሌላ አክሊል ነካሁ÷ነገር ግን የዚህ አክሊል ከላዩ ላይ ያሉትን እንቁዎች ሁሉ ማጣት ሲጀምር አየሁ። "*ጌታ ሆይ! ይህንን አክሊል ለእኔ አታድርገው!*" ጌታም አለ "***ተመልከች አገልጋዬ÷በወይን እርሻዬ መሥራት መቀጠል ለማይፈልጉ እንደዚህ ነው የሚሆንባቸው÷ እኔን ማመስገን ትተው ጀርባቸውን ሊሰጡኝ ለወደዱ÷ አክሊላቸው እንዲህ ነው የሚሆነው። ከእንግዲህ በወይን እርሻዬ መሥራት ለማይፈልጉ÷ አክሊላቸው እንዲህ ነው የሚሆነው።***" (ራዕይ 3:11)

ከዚያም ጌታ ወደ ሌላ የሚያምር ቦታ ወሰደኝ÷እናም ብዙ የተኙ ሰዎችን አየሁ። በጣም ነጭ እጀጠባቦችን ለብሰዋል። እንዲህ አልኩ "*ጌታ ሆይ÷ እነዚህ ሁሉ ሰዎች እነማን ናቸው?*" ጌታም መለሰ "***ተመልከች አገልጋዬ÷ እዚህ ያሉት እነዚህ ሁሉ ሰዎች በምድር የሞቱ ናቸው÷እናም አሁን በገነት እረፍት ላይ ናቸው÷ እናም መለከቱ እነዲነፋ ትእዛዝ ስሰጥ÷የሞቱት መጀመሪያ ይነሳሉ እና ከዛም በምድር ላይ ያሉት።***" በጣም ብዙ ሰዎች ነበሩ÷እና ልብሳቸው በጣም ነጭ ነበር። (1ኛ ተሰሎንቄ 4:16-17)

ማንም ሰው ከማንም ጋር አያወራም ነበር፤ ዝም ብለው ተኝተዋል÷ጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ። እናም ጌታ ይህን ነገረኝ "***አገልጋዬ እነርሱ እረፍት ላይ ናቸው÷ነገር ግን መለከቱ ሲነፋ÷እነዚህ ቀድመው ይነሳሉ÷እናም ከዛ በምድር የሚቀሩት ከእኔ ጋር ለመሆን ከእነርሱ ጋር በአንድነት ወደ ላይ ይነሳሉ። እናም ከዛ የበጉን ሠርግ ማክበር እንችላለን።***"

[ተፈጸመ]

*በ ያኔት ባልዴራስ ካኔላ (Jannet Balderas Canela)*

ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ትርጉም ሙሉነህ አዲሱ አብዲሳ
Translated to Amharic by Muluneh Addisu Abdissa, matoughen@gmail.com